# በአንድ ፍላጻ ሶስት ጫፎች፡-

## ምስክርነት ከወንጀለኞች አንደበት?

(በህያዉ ቃል)

(ካለፈዉ የቀጠለ )

ለተጠቀሱት ከጥንድ በላይ ለሆኑ ተልዕኮዎች መሳካት ፡ ሻምበል ተስፋዬ ከይሉኝታ በላይ (ከታሪክም ከታሪክ ቀመስም ደራሲ ሥነምግባር ተፋርሰዉ ) እንደደከሙበት በግልጽ የሚያመለክተዉ ደግሞ በ"መጽሐፋቸዉ " ዉስጥ ከመነሻዉ እስከ መደምደሚያዉ መለዮ ለባሹና ከዚያም መለዮዉን ወርዉሮ ከሲቪል ለመመሳሰል የቃጣዉ ደርግ 17 ዓመታት ባስቆጠረዉ የአገዛዝ ዘመኑ ላደረሰዉ የአገር ዉድቀትና የትዉልድ ዕልቂት አንዳችም የቡድን ተጠያቂነት እንደማይኖርበት (ይልቁኑ ተጠያቂዎቹ ምሁራን ፖለቲከኞች፡በተለይም ኢሕአፓ መሆናቸዉን ) በይፋ መከራከራቸዉ ነዉ ። በዚህም ደርግንና በላኤሰብ አባሪዎቹን ከደም ጭቅቅት በማለቃለቅ በሰማዕቱ እግር ሊያቆሙአቸዉ ይዳዳቸዋል ። ይህን ለማድረግም ሆነ "ቀይሽብር " የሚሉት አገርንና ትዉልድን የፈጀ መዐት ፡ አገርን ከጥፋት ለመታደግ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የተደረገ "ተጋድሎ" ነዉ ከሚል ድምዳሜ ለመድረስ መቼም ሻምበሉን መሆን ፡ መርማሪዉን ተስፋዬን ሆኖ መገኘትን በግድ የሚሻ ጉዳይ ነዉ ።

እዚህ ላይ ከሻምበል ተስፋዬ ጉደኛ "ምስክርነት"ና ጥብቅና ጋር የሚመሳሰል አንድ የሰነበተ ድርጊት ታወሰኝ ። ሰዉዬዉ በዘመነ ደርግ ጎምቱ ባለሥልጣን ነበሩ ።

"ነበሩ " መባሉ ዛሬ በሕይወት መኖራቸዉን አሌ ለማለት አይደለም ፡- አሉ - በስደት ። በወቅቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማታዉ ፈረቃ የሚከታተሉትን የሕግ ትምሕርት ለማጠናቀቅ የመመረቂያ ጽሁፍ ለማዘጋጀት ተፍ ተፍ በማለት ላይ ነበሩ ። ለዚሁ ዝግጅት አስቀድመዉ ለጥናት ጽሁፉ የመረጡትን ሕግ ቀመስ ርዕሰ ጉዳይና ርዕስ ለተመደበላቸዉ አማካሪ ማቅረብና ማስጸደቅ ነበረባቸዉ ። ለጥናታቸዉ መርጠዉ በእንግሊዝኛዉ ያቀረቡት ርዕስ ትርጓሜ ፡ " የቀይ ሽብር ሕጋዊነት -- በኢትዮጵያ " የሚል ነበር ። አማካሪያቸዉ በጊዜዉ የመጣባቸዉን ሳቅ መቻል የግዳቸዉ ቢሆንም (ሰዉዬዉ ከግንድ የሚያላጋ ሥልጣን ነበራቸዉና ) በታላቅ ትህትናና ጽሞና ከነወረቀታቸዉ የመለሱላቸዉ ነገር ፡ "ሽብር" ና "ሕጋዊነት " ከጽንሰ ሃሳብ አንስቶ የሞትና የሕይወትን ያህል ርስበርሳቸዉ ተገዳዳሪ መሆናቸዉን በአጽንኦት የሚያስገነዝብ ነበር ።( ዘመን ሽሙጡ አያልቅበት ሆኖ ነዉ መሰል ዛሬ ላይ የትናንቶቹ ሰዉ አራጆች ዐይን ያወጣ ድርቅናቸዉ ወሰን አጥቶ ፡ ድርሳነ ወንጀሎቻቸዉን እንደመጽሓፍ ጠርዘዉ ሊቸበችቡልን ገበያ መሃከል ቆመዉልናል ።) ይህ ሽብርና ሕግ ርስበርስ ያላቸዉ ተቃርኖ ሻምበሉን ጸሀፊ በቁም (ቢያንስ ጽሁፋቸዉ ሲወጠን አማካሪያቸዉ እንደ ነበሩት እንደ ካሣዬ አራጋዉ ድንገተኛ ሞት እስኪገላግላቸዉ ድረስ ) የሚከሰስ ፡ በየምዕራፉቱም የሚኮንናቸዉ አይነተኛ የክስ ቻርጅ ሆኖ ይኖራል።

ሻምበል ተስፋዬ ታሪክ ተረስቶ እንዳይቀር የነበራቸዉ ፍላጎት መነሳሻ እንደሆናቸዉ ደጋግመዉ ይነግሩናል ። እንደ አንድ የታሪክ ጸሓፊ ግን ታሪክ ሆኖ ያለፈን ክስተት ፡ (ያዉም ከሰላቢዉ ወገንና ከሰለባዉ ትዉልድ ሕያዉ ምስክር ባልታጣበት ሁኔታ) በተፈጸመበት መልኩ ሲመዘግቡ በፍጹም አናስተዉላቸዉም ። በምትኩ ፡ ያለአንዳች ማስረጃ በራሳቸዉ ችሎት አቁመዉ የፈረዱበትን ትዉልድና የፖለቲካ ድርጅት ዛሬም መልሰዉ ራስ ራሱን ይቀጠቅጡታል ። የታሪክ አጋጣሚ ሆነና ጨካኙን ወታደራዊ አምባገነንነት እስከፍጻሜዉ ድረስ የታገለና ሕዝቡን በግንባር ቀደምነት ያታገለ ትዉልድና ድርጅቱ - ኢሕአፓ ዛሬም ሥልጣን ላይ ለመቆናጠጥ በለስ ከቀናቸዉ ጠባቦችና ፀረ- ኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር የሞት- የሽረት ትንቅንቅ ላይ ይገኛሉ ። ከዚህ ገሃድ እዉነት አንጻር ፡ ሻምበሉና አያሌ መሰሎቻቸዉ ፡ አነሰ ቢባል በምንዝር

“ጅራፍ ተሸካሚነት” ደረጃ የዉስጥ ገላዉን በገለበጡትና በየጥሻዉና በየገላጣዉ ረፍርፈዉ በድኑን በአፈር ጎድፋሪ መኪና ባለባበሱት በሳል - ግን በዕድሜ እንቦቀቅላ የሕዝብ ልጅ ላይ እንዲያ ያስጨከናቸዉን መነሾ (ያዉስ የሰዉን ልጅ ያህል ፍጡር ለማጥፋት ምን ያህል ምክንያት ይበቃል????) በተጨባጩ አመልክተዉ ለደረሰዉ ጥፋት የየድርሻቸዉ ሃላፊነት እንዳለባቸዉ ጠቆም እንኩዋ አያደርጉም ።( ቀድሞ ነገር በአገር ደረጃ ስለተካሄደና በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖች ጭዳ ስለተደረጉበት ክስተት ይፋ ምስክርነቱን በወረቀት ላይ የሚያሰፍር አንድ የታሪክ ጸሓፊ ፡ “------ዜጎች ተጨፍጭፈዋል ፡ ጨፍጫፊዎቹ ግን በቂ ምክንያት ስላላቸዉ ተጠያቂዎቹ ተጨፍጫፊዎቹ ናቸዉ ።” ለማለት የሚያበቃ መብት ይኖረዉ ይሆን?????) ለመሆኑ ይሉኝታና ጸጸት የት ገቡ ለሚል ጠያቂ “ንጹህ ሕሊና በሌለበት እንዴት ይኑሩ ?” ብሎ የሚመልስ ሰዉ በማስረጃነት “ምስክርነት”ንና አጠናቃሪዉን ሻምበል ቢጠቅስ ስሕተት ይሆንበታልን?? ፍትህ-ርትዕን ለማስፈን የሚያስችል ማሕበራዊ ለዉጥን ካስከተለ በሰፈሩበት ቁና መሰፈር አይቀርምና መጻዒዉን ጊዜ በፍርሃት ርደዉ የሚጠብቁ ተስፋዬን መሰሎች በዚህ ዓለም ላይ ይንከላወሳሉ። ያለፈዉንና ጉደኛዉን የዕድሜያቸዉን ገበና ለመጋረድም የሓሰት ድሪቶአቸዉን ይቀጣጥላሉ። በዚህም ብቻ አያቆሙም። በሞራልና በሕግ የሚገዛ ሕልዉና የሌላቸዉ በሚመስል ሁኔታ አገርንና ታሪክን እያነኩዋኮተ የዉር ድንብሩን ለሚንደፋደፍ የጫካ ሥርዐት ሎሌነት አድረዉ ዳግም በጥፋት አገልጋይነት በመሰለፍ በቀረችዉ የዕድሜአቸዉ ጠርዝ ይንጠራወዛሉ ። ሕዝብና አገር ግን ሁሌም ሕያዉ ናቸዉና የሚሆነዉን ሁሉ ይታዘባሉ ። ሁኔታዎች በፈቀዱላቸዉ መጠንም እዉነተኛዉን በገሃድ ይመሰክራሉ ።

ሻምበል ተስፋዬ ዓላማቸዉን “ለትዉልድ አስቀር ብዬ “ በሚል ይግለጹት እንጂ ለዚሁ ዉጥን ሥራ ዋቢ እንዲሆኑዋቸዉ የተጠቀሙባቸዉን መረጃዎች በማሰባሰቡ ረገድ ግን ሚዛናዊ ሆኖ ለመገኘት በፍጹም አይጨነቁም ። ይህ ግድየለሽነታቸዉ ግን በገበያ ላይ ያዋሉትን ጥራዝ ላገላበጠ ሁሉ የሚጠቁመዉ አንድ ግዙፍ እዉነት ይኖራል ፡- ጸሓፊዉ ገለልተኛ ሳይሆኑ ከሁሉ አስቀድመዉ የደረሱበትን የግል ድምዳሜ ይዘዉ የተነሱ መሆናቸዉን ። በመረጃዎቹ አጠቃቀምና አተረጉዋጎምም በኩል ያዉ ናቸዉ ። እጽፈዋለሁ ብለዉ በታጠቁለት ታሪክ ዉስጥ በጉልህ የሚታዩትን ሐይሎች በእኩለ አይን አያዩዋቸዉም። አተያየታቸዉ በአድልዎ የተጠናበረ ነዉ። ገና ከመነሻቸዉ “ጥፋተኛ “ ብለዉ የወሰኑበትን (ፍርደኛ ) ወገን ነጻ የሚያወጣ መረጃ ብዕራቸዉ እያሠፈረ እንኩዋ የቀድሞዉ የግል ዉሳኔያቸዉ ከቶ አይቀየርም ።

“ምስጋና “ በሚል ንዑስ ርዕስ ባቀረቡት መንደርደሪያ ዉስጥ ራሳቸዉ እንደሚነግሩን “ብዙ ሰዎችን “ አነጋግረዋል ። በዝርዝርም የደርግን ቱባ ቱባ ሹማምንት ፡ (በወቅቱ በሰዉ ዘር ማጥፋት ወንጀል የታሠሩ ) ከአናቱ ከሻምበል ፍቅረሥላሤ ወግደረስ ይጀምሩና በተዋረድ እስከ ተሾመ ገ/እግዚአብሔር ፡ ተፈራወርቅ አያሌዉና ተኮላ ማሞ ድረስ በስም ያሰፍራሉ ። በአጠቃላይ ከ31 በላይ የደርግን ባለጊዜዎች አነጋግረዋል ። ከነዚህ ጋር እኩል ቆጥረዉ ዝርዝሩ ዉስጥ ባያስገቡዋቸዉም ሌሎች ቁጥር ያላቸዉን የቀበሌ ታጣቂዎችንም አስተያየትና ገለጻ አስፍረዋል ። የሚገርመዉ ጉዳይ ; ያን ያህል ጊዜ ወስደዉ ተሾመ ገ/እግዚአብሄርን የመሳሰሉ የማእከላዊ ወንጀል ምርመራ ጭራቆች ያነጋገሩት ሻምበል በአንጻሩ ግን ከኢሕአፓ ወገን አንድ ሰዉ እንኩዋ ለማነጋገር አልፈለጉም ። ምክንያቱ ግልጽ ነዉ ፡ ኢሕአፓ በመርማሪዉ ሻምበል የግል ችሎት ከድርሰቱ ጅማሮ በፊት ጥፋተኛ ተደርጎ ተፈርዶበታል ። ገበያ ላይ ካዋሉት ጥራዝ የፊት ለፊት ሽፋን አልፈዉ ወደዉስጥ ብዙም ገጾች ሳይርቁ ጀምረዉ የሚወቅጡ የሚሰልቁትም ይህንኑ ጉዳይ ነዉ ። የጽሁፍ ሥራቸዉ ከተጠናቀቀ በሁዋላ ብቻ “የደርግ የኢሕአፓንና የመኢሶን አመለካከት ደጋፊ ናቸዉ “ ያሉዋቸዉን በጣም ጥቂት ሰዎች አስነብበዉ ሃሳባቸዉን ለማግኘት መሞከራቸዉን ይነግሩናል ። (በሮማዉያን ቁጥር ፡ ገጽ 4 ) ። ለመሆኑ ምን ምላሽ አግኝተዉ ይሆን ? መልሱን አናገኘዉም ። እዚህ ላይ ሀገራዊዉን ብሒል ትንሽ ለወጥ እናድርገዉና “በኮሎኔሉ ጊዜ የደነቆረ የሁሌም መሃላዉ “ ነጻ ርምጃ “ ነዉ ፡ “ብለን እንተርት። ለስላቅ ብቻ ብለን ያልነዉ ግን አይሆንም ።

– ይቀጥላል -